ይድረስ ለእማምዬ ኢትዮጵያ፤
አሁንስ ይበቃል፤
አሜኬላ ማብቀል።

30 40 አመት፤ አሜኬላ አብቅለሽ
የልጆችሽን የደም ጎርፍ፤ ማየቱ ሰልችቶሽ
ይበቃል በማለት ደርጎችን (ፋሽስቶች) አባረሽ
እባቡን ወያኔ ባለቀን አድርገሽ፤
መርዙን አሰራጭቶ፤ ታመሱ ልጆችሽ
አሁንስ ይበቃል፤ ነቀርሳን ማብቀልሽ

እማማዬ የኛ እናት፤ ሁኚ እንደ ጥንትሽ
በግፍ ለታጨዱት፤ ለወጣቱ ብለሽ
ከማፍቀርም በላይ፤ ህይወት ለለገሱሽ
ለጀግናው ቴዎድሮስ፤ ራሱን ለሰዋልሽ
ለጀግናዋ ባልደረባ፤ ለተዋቡ ብለሽ
ለዛ ለታማኙ፤ ለገብርዬ ብለሽ
ለአሉላ አባነጋ፤ ለዘርአይ (ደረስ) ብለሽ
ለዑመር ሰመተር፤ ለአባ ባልቻ ብለሽ
እረንጅዴ ቢጫ ቀዩን፤ ጥለትሽን ለብሰሽ
የኢትዮጵያውነት ወኔ፤ እንዲያገረሽ አርገሽ
ይዝመቱ ወያኔ ላይ፤ አንድ ሁነው ልጆችሽ
የዘር መርዙን ያጥፉ፤ እንዲመለስ ክብርሽ
ለምኚ ፈጣሪን፤ ጠብቆ ላቆየሽ
እንፀልይ ለአምላክ፤ እንዲታደግሽ
ዱአ እናደርጋለን፤ ጠብቆ እንዲያቆይሽ

የጎላ ምንጭ
July 2016